**የገንዘብ ሚኒስቴር**

**MINISTRY OF FINANCE**

# በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች ለሚቀጠሩ ጊዜያዊ ሰራተኞች የደመወዝ ክፍያ አተገባበር መመሪያ ቁጥር 1125/2018

**መጋቢት 2018 ዓ.ም**
**March 2026**



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

# በልማት አጋሮች ድጋፍ በሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ለሚቀጠሩ ጊዜያዊ ሰራተኞች የደመወዝ ክፍያ አተገባበር መመሪያ ቁጥር 1125/2018

የገንዘብ ሚኒስቴር የውጭ ሀብትን እንዲያሰባስብና የተሰበሰበው ሀብት ለታለመለት ዓላማ ተግባራዊ መሆኑን እንዲከታተል ሥልጣን እና ተግባር የተሰጠው በመሆኑ፤

በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መስሪያ ቤቶች በሚተገበሩ ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች ለሚቀጠሩ የጊዜያዊ ቅጥር ሰራተኞች ፍትሃዊና ወጥ ስርዓት በመዘርጋት የተጣጣመ የደመወዝ አተገባበር በግልፅ እንዲቀመጥ በማስፈለጉ፣

የስራ መደቦችን በመለየት ተመሳሳይ ባሕሪይ እያላቸው በተለያዩ ስያሜዎች የሚጠሩትን መደቦች ወጥ የስራ ደረጃ እና ስያሜ እንዲኖራቸው እንዲሁም ዝቅተኛ ተፈላጊ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት እንዲኖር በማስፈለጉ፣

የጊዜያዊ ቅጥር ሰራተኞች የተጣጣመ ደመወዝን በተመለከተ በሁሉም የፌደራል መሥሪያ ቤቶች እና ክልሎች ወጥና ግልፅ የሆነ አፈፃፀም እንዲኖር ለማድረግ፣

ተግባራዊ ሲደረግ በነበረው መመሪያ ያልተካተቱና ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮችን በማካተት እንዲሁም ነባራዊ የገበያ ሁኔታን ታሳቢ በማድረግ ነባሩን መመሪያ መሻር በማስፈለጉ፤

የፌዴራል የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19(4) መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መስሪያቤቶች በሚተገበሩ ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች ለሚቀጠሩ ጊዜያዊ ሰራተኞች የደመወዝ ክፍያ አተገባበር መመሪያ ቁጥር 1125/2018"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

1) **"የመንግሥት መሥሪያ ቤት"** ማለት ራሱን ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመና ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በክልል መስተዳድር ወይም በከተማ አስተዳደር ስር የሚገኝ መሥሪያ ቤት ነው፤

2) **"ሚኒስቴር"** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፤

3) **"የልማት አጋር"** ማለት ለልማት ፕሮግራሞ ወይም ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የፋይናንስ፣ የቴክኒክ እና የዓይነት ድጋፍ በብድር ወይም በዕርዳታ መልክ በመስጠት የመንግሥትን የልማት አጀንዳ የሚደግፉ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት፣ መንግሥታት፣ ቻሪቲዎችና ፋውንዴሽኖች ናቸው፤

4) **"ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት"** ማለት በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌደራልም ሆነ በክልል መንግሥታት መሥሪያ ቤቶች ባለቤትነትና አስፈፃሚነት በረዥም፣ በመካከለኛና በአጭር ጊዜ የሚተገበር ነው፤

5) **"ጊዜያዊ ሰራተኛ"** ማለት በፌደራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 አንቀጽ 2(2) እንዲሁም በፌዴራል እና በክልል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የጊዜያዊ ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ በተሰጠው ትርጉም መሠረት በመንግሥት መሥሪያ ቤት የዘላቂነት ባህሪ በሌለው ስራ ላይ ወይም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው። ሆኖም፤

   ሀ) በቀን ሂሳብ እየተከፈላቸው የሚሰሩ የቀን ሰራተኞችን፤

   ለ) በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የሙያ ሥልጠና ወይም የስራ ልምድ ለማግኘት የሚመደቡ ተለማማጆችን፤

   ሐ) ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር በገቡት ውል ዋጋ እየተከፈላቸው በራሳቸው የንግድ ስራ ወይም የሙያ ኃላፊነት የሚሰሩ ተቋራጮችን፤ እና

   መ) ባላቸው ልዩ ዕውቀትና ችሎታ ምክንያት ከመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ጋር በሚገቡት ውል መሰረት ዋጋ እየተከፈላቸው በትርፍ ጊዜያቸው የሚሰሩ ባለሙያዎችን አይጨምርም።

6) **"የበላይ ኃላፊ"** ማለት ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች የሚተገበሩበት የፌደራልም ሆነ የክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤትን በበላይነት የሚመራ ኃላፊ ሲሆን ምክትል ሃላፊን ይጨምራል።

7) **"የሥራ መደብ"** ማለት በአንድ በልማት አጋር በሚደገፍ የልማት ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት ተቀጥሮ በሚሰራ የጊዜያዊ ሰራተኛ ሙሉ የሥራ ጊዜ እንዲከናወኑ



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

በቀጠረው አካል ወይም የመንግሥት መስሪያ ቤት የተሰጡ የሥራ መዘርዝሮች እና ተግባርና ኃላፊነቶች ናቸው፤

8) **"የስራ ደረጃ"** ማለት በአንድ የሥራ ምድብ ባሉ ተመሳሳይ የስራ መደቦች ውስጥ የሚገኙ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ያሉ የሥራ መደቦች ናቸው፤

9) **"የስራ ምድብ"** ማለት በስራ ባህሪያቸው ተቀራራቢ የሆኑ የስራ መደቦች በወል የሚካተቱበት ማዕቀፍ ወይም ምድብ ነው፤

10) **"ደመወዝ"** ማለት በአንድ ጊዜያዊ የስራ መደብ ለተቀጠረ ሰራተኛ ከመነሻ እስከ ጣሪያ ድረስ ለስራ መደቡ የተወሰነ ክፍያ ነው፤

11) **"የተጣጣመ ደመወዝ"** ማለት ተመሳሳይ ለሆኑ የስራ መደቦች በፕሮግራሞች ወይም በፕሮጀክቶች ዓይነቶች እና በተለያዩ የልማት አጋሮች መሰረት የማይለያይ እና ወጥ የሆነ ክፍያ ማለት ነው፤

12) **"ጥቅማጥቅም"** ማለት ለስራ መደቡ ከሚከፈለው ደመወዝ በተጨማሪ ሠራተኞችን ለማበረታታት በገንዘብ ወይም በዓይነት የሚሠጥ ማትጊያ ወይም ማበረታቻ ነው፤

13) **"ዝቅተኛ ተፈላጊ ዝግጅት"** ማለት የጊዜያዊ ሰራተኞችን ባሉ ክፍት የስራ መደቦች ለመቅጠር፣ ለማሳደግ ወይም ለመመደብ የሚያስፈልግ ዝቅተኛ ተፈላጊ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት ነው፤

14) **"መስፈርት"** ማለት ዝቅተኛ ተፈላጊ ዝግጅትን አሟልተው በስራ መደብ ለመቀጠር በዕጩነት የቀረቡ የጊዜያዊ ወይም የኮንትራት ሰራተኞችን ችሎታና ብቃት በመመዘን ብልጫ የሚያገኙትን አሸናፊዎች በክፍት የስራ ቦታው ለመመደብ የሚያገለግል ማወዳደሪያ ነው፤

15) **"እርከን ጭማሪ"** ማለት የጊዜያዊ ሰራተኛው በተቀጠረበት የሥራ መደብ ሲከፈለው ከነበረው ደመወዝ ቀጥሎ የሚገኘው የደመወዝ ዕርከን ክፍያ ሲያገኝ ነው፤

16) በዚህ መመሪያ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1) ይህ መመሪያ በሁሉም የልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚካሄዱ ፕሮግራሞችን ወይም ፕሮጀክቶችን ለመተግበር አዲስ ጊዜያዊ የስራ ቅጥር ሲፈጽሙ፣በተሻሻለው ደመወዝ መሰረት የነባር የጊዜያዊ ሠራተኞችን ውል ሲያድሱ፣የሚመለከታቸውን ነባር ጊዜያዊ ሰራተኞችን አዲስ በተጨመረው የመደበኛ የፕሮጀክት ሰራተኞች ምድብ ስር በተዘረዘሩት የስራ መደቦች መሰረት የስራ መደብ ስያሜዎችን ሲያስተካክሉ፣ እና የደመወዝ ዕርከን ጭማሪ ሲያካሂዱ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በሚከተሉት ላይ ይህ መመሪያ ተፈፃሚ አይሆንም፤

ሀ/ በመመሪያው የተመለከተው ደመወዝ በቁርጥ ዋጋ እና በውስን ጊዜ ውስጥ መተግበር ያለባቸውን የተለዩ ቁልፍ ተግባራትን ለማሰራት በአገልግሎት ግዥ አግባብ የሚቀጠሩ አማካሪዎችን በተመለከተ፤

ለ/ በመንግሥት መስሪያ ቤቶች በመደበኛ የሥራ መደቦች የደመወዝ እርከን ላይ የልማት አጋሮች ለፕሮጀክቶች ከሚመድቡት የኦፕሬሽን ወጪዎች ላይ በማከል አንድ ወጥ የደመወዝ አከፋፈል ሥርዓት ተግባራዊ እንዲያደርግ በልዩ ሁኔታ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ተፈቅዶ ተግባራዊ የሚያደርግ መስሪያ ቤትን በተመለከተ፤

ሐ/ በልማት አጋሮች የውስጥ አሠራርና ደንብ፣ የደመወዝ ክፍያ ወሰን፣ ጥቅማጥቅም እንዲሁም የቅጥር ሥርዓት በቀጥታ ተቀጥረው በመንግሥት ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች ላይ የሚሰሩና ተጠሪነታቸውም ለልማት አጋሮቹ የሆኑ ተቀማጭ ሰራተኞችን በተመለከተ፤

3) ይህ መመሪያ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያወጣው የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የጊዜያዊ ሰራተኞች ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ እና የክልል መንግሥታት ያወጧቸው የጊዜያዊ ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያዎች ውስጥ ከተካተቱ ድንጋጌዎች ጋር ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የሥራ ምድብ ስያሜዎች መግለጫ</u>

### 4. <u>የስራ ምድብ</u>

1) በተለያዩ ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች ያሉ የጊዜያዊ የስራ መደቦች ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ መደቦች፣ ከድጋፍ ሰጪ እስከ ልዩ ሙያተኞች በዓይነታቸው እና ተፈላጊ ችሎታቸው የተለያዩ በመሆናቸው የስራ መደቦቹን በአራት ዋና ዋና የስራ ምድቦች በማጠቃለል በውስጣቸው በባህሪያቸው ተቀራራቢ የሆኑ ልዩ ልዩ የስራ መደቦችን ይይዛሉ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት አራቱ የስራ ምድቦች ልዩ አማካሪዎች፤ የዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች፣ የፕሮጀክት ሰራተኞች፣ እና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ናቸው፡፡



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

3) ልዩ አማካሪዎች እና የዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች ውስን በሆነ መጠን እና የመስሪያ ቤቶችን ልዩ ፍላጎት መሰረት በማድረግ ውስብስብ የማማከር እና ሙያዊ ዕገዛ ተግባራትን ለማከናወን በመንግሥት የቴክኒክ ባለሙያዎች አቀጣጠር እና አጠቃቀም ማዕቀፍ መሰረት በልዩ ሁኔታ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ የሚቀጠሩ ይሆናሉ፡፡

4) የፕሮጀክት ሰራተኞች እና የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኞች የፕሮጀክት አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ፕሮጀክቶችን የመተግበር፣ የማስተዳደር፣ የመከታተል እና ድጋፍ የማድረግ አቅማቸውን ለማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተጠቀሱትን ዋና ተግባራት እንዲሁም ፕሮጀክት-ነክ ተግባራት እንዲያከናውኑ የሚቀጠሩ ይሆናሉ፡፡

5) የፌዴራልና የክልል የፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት ፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ከላይ በተጠቀሰው አግባብ የጊዜያዊ ሰራተኞችን ከመቅጠራቸው በፊት የፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት ስራዎች በመደበኛ የመንግሥት ሰራተኞች ሊሸፈኑ ወይም መከናወን አለመቻላቸውን በማረጋገጥ ሲታመንበት ቅጥሩን ማከናወን አለባቸው፡፡

## 5. ልዩ አማካሪዎች

1) ልዩ አማካሪዎች እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ የመስሪያ ቤቶችን የበላይ አመራሮችን ተቋማዊ በሆኑ የፖሊሲ እና ስትራቴጂክ-ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዲያማክሩ እንዲሁም ልዩ ሙያቸውና ልምዳቸውን በመጠቀም ውስብስብ ስራዎችን እንዲያከናውኑ በልዩ ሁኔታ የሚቀጠሩ ናቸው፡፡

2) በልዩ አማካሪዎች ምድብ የሚካተቱት ከዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች በላቀ ደረጃ ዕውቀትና ክህሎት እንዲሁም ልምድ የሚጠይቁ የአማካሪነት ስራዎችን የሚሰሩ ናቸው፡ :

## 6. ዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች

1) በዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች ምድብ ውስጥ የሚገቡት የጊዜያዊ ሰራተኞች የሙያ አገልግሎታቸው በተቀጠሩበት ፕሮጀክት ሳይወሰን ወይም በአንድ ፕሮጀክት ሳይገታ በቀጣሪው መስሪያ ቤት ውስጥ ባሉ የተለያዩ የስራ ዘርፎች ላይ ሙያዊ ግልጋሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡

2) የዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች የስራ ወሰን ሰፊና እንደሙያቸው ከአንድ ፕሮጀክት በላይ በሆኑ ጉዳዮች የተቋሙን ግብና ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ስራዎችን በቀጥታ እንዲያከናውኑ በልዩ ሁኔታ የሚቀጠሩ ሠራተኞች ናቸው፡፡



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

## 7. የፕሮጀክት ሰራተኞች

1) የፕሮጀክት ሰራተኞች ባላቸው የተለየ ክህሎት እና ሙያ እንደየፕሮጀክቱ ባህሪ በቀጥታ በፕሮጀክቱ ትግበራ ላይ የሚሳተፉ ሲሆን ለፕሮጀክቱ ውጤቶች መሳካት ቀጥተኛ ሙያዊ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

2) በዚህ ምድብ የሚካተቱት በፕሮጀክቱ በዕቅድ የተያዙ ተግባራትን በማከናወን የፕሮጀክቱን ዓላማና ውጤቶች ለማሳካት ሙያዊ አገልግሎትን እንዲሰጡ የሚቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው፡ ፡

3) የፕሮጀክት ሰራተኞች ምድብ በመደበኛነት ተለይተው የሚታወቁ፣ የተለመዱና በበርካታ ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች ላይ በተደጋጋሚ የሚስተዋሉ የስራ መደቦችን በዝርዝር ያቀፈ ነው፡፡

4) የፕሮጀክት ሰራተኞች ምድብ ብዙም የማይታወቁ፣ ያልተለመዱ እና አዲስ ሊያስፈልጉ የሚችሉ የስራ መደቦችን ሊያጠቃልል በሚችል መልኩ "ሌሎች ሲኒየር የፕሮጀክት ሰራተኞች" የሚል የስራ መደብን ያካትታል፡፡

5) በስም ተጠቅሰው ከተዘረዘሩት የስራ መደቦች ውጪ የዚህን ምድብ ትርጓሜ የሚያሟሉ የስራ መደቦች በሙሉ "ሌሎች ሲኒየር የፕሮጀክት ሰራተኞች" እና "ሌሎች የፕሮጀክት ሰራተኞች" በሚል በተጠቀሰው የስራ መደብ ውስጥ ይጠቃለላሉ፡፡

6) ቀጣሪ መስሪያ ቤቶች በስም ተጠቅሰው ከተዘረዘሩት የስራ መደቦች ውጪ በሌሎች የስራ መደቦች ባለሙያዎችን መቅጠር ሲያስፈልጋቸው በሚዘጋጀው ቢጋር መሰረት የስራ መደቡን መጠሪያ በመጥቀስ ቅጥር መፈጸም ይችላሉ፡፡

## 8. ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

ይህ ምድብ ለፕሮግራሙ ወይም ለፕሮጀክቱ መሳለጥ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ የሚሰጡ የኮንትራት ሰራተኞችን የሚይዝ ነው፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለ ቅጥር፣ ደመወዝ፣ እርከን እና ጥቅማጥም

## 9. የደመወዝ አተገባበር

1) በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች የጊዜያዊ የሰራተኞች ደመወዝ በዚህ መመሪያ አባሪነት ከሰንጠረዥ 1 እስከ 4 በቀረበው የደመወዝ ስኬል መሰረት በብር ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2) የጊዜያዊ ሰራተኞች ተቀጥረው እየሰሩበት ያለው የስራ ደረጃ እና የደመወዝ እርከን ሳይለወጥ በዚህ መመሪያ ለተመሳሳይ የስራ ደረጃ እና የደመወዝ እርከን የተቀመጠውን የደመወዝ መጠን ያገኛሉ፡፡



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

## 10. <u>የአዲስ ሰራተኛ ቅጥር</u>

1) በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚገኙ የፕሮጀክት ፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በልማት አጋሮች ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችን ወይም ፕሮጀክቶችን ለመተግበር በቅድሚያ በመደበኛው መዋቅር ያለውን አቅም ታሳቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም በመደበኛው መዋቅር እና ሰራተኞች መተግበር የማይችሉ መሆናቸው ሲታመንበት ለደመወዝ የሚውለው በጀት በፕሮጀክት ዕቅዶች ውስጥ መካተቱን በማረጋገጥ ለፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች ትግበራ የሚያግዙ ሰራተኞችን በዚህ መመሪያ መሰረት በጊዜያዊነት መቅጠር ይችላሉ፡፡

2) በዚህ መመሪያ አዲስ ቅጥር ተፈጻሚ የሚሆነው ለስራ መደቡ የተወሰነውን ዝቅተኛ ተፈላጊ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት የሚያሟሉትን በማወዳደር ለሥራ መደቡ የተወሰነውን መነሻ ደመወዝ በመክፈል ይሆናል፡፡

3) የጊዜያዊ ሰራተኞች ቅጥር አፈጻጸም በመመሪያው ክፍል ሁለት በተገለጹት የስራ ምድቦች ትርጓሜዎች በመነሳት እና በአባሪው ከሰንጠረዥ 1-4 በተገለጹት የስራ መደብ ስያሜዎች መሰረት ሰራተኞቹ እንዲያከናውኑት ከሚጠበቁት ተግባራት ጋር በማዛመድ የጊዜያዊ ስምምነት በመፈጸም ይሆናል፡፡

4) አዲስ ቅጥር የሚፈጸምበት የስራ መደብ የስራ ደረጃ ያለው ከሆነ በዋነኛነት ፕሮጀክቱ የሚፈልገውን የስራ መጠንና ውስብስብነት ታሳቢ በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የሥራ ደረጃ ከተዘረዘሩት የስራ መደቦች መካከል ለስራው የሚመጥነውን በመምረጥ እና ለሥራ መደቡ የተወሰነውን መነሻ ደመወዝ በመክፈል ነው፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሲሆን ተወዳዳሪው ያለውን አግባብነት ያለው የስራ ልምድ፣ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች አንፃር ያለው ልዩ ዝግጁነት እና በገበያው ያለው ተፈላጊነት እንዲሁም ለስራ መደቡ በዕቅድ ከተያዘው በጀት አንፃር እየታየ ደመወዙ ከስራ መደቡ ከመነሻ እስከ መጨረሻው ዕርከን ድረስ ባለው ውስጥ በድርድር ሊወሰን ይችላል፡፡

## 11. <u>የእርከን ጭማሪ</u>

የእርከን ጭማሪ በየዓመቱ ተግባራዊ የሚደረግ ሆኖ የጊዜያዊ ሰራተኛው ዓመታዊ የተጠቃለለ የስራ አፈጻጸም በቅርብ የስራ ኃላፊው ተሞልቶ ከተመዘነ በኋላ ውጤቱ 70 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ከሆነ ብቻ የሚቀጥለውን ዕርከን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

## 12. <u>የስራ ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ</u>

በአሰሪው መስሪያ ቤት እና በሰራተኛው መካከል የተገባው ውል በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊቋረጥ ይችላል፤

1) አሰሪው መስሪያ ቤት እና ሰራተኛው የውል ጊዜ ከማለቁ በፊት ለማቋረጥ ሲስማሙ፣



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

2) የውሉ ዘመን ከመድረሱ በፊት ስራው የተጠናቀቀ እንደሆነ ወይም በፋይናንስ እጥረት ምክንያት ቀጣሪው መስሪያ ቤት ውል ማራዘም የማይችል ከሆነ፤

3) ቀጣሪው መስሪያ ቤት የሚተገብረው የፕሮጀክት ተግባራት በመቀነሱ ምክንያት የሰው ኃይል መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና ውሉን ማራዘም የማይችል ከሆነ፤

4) ውሉን ለማቋረጥ ቀጣሪው ወይም ተቀጣሪው የሰጠው የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ጊዜ ሲያበቃ፣

5) ተቀጣሪው ለተቀጠረበት የሚፈለግበትን ዕውቀት በስራ ያላሳየ ወይም ስራውን በሚገባ ለማከናወን ያልቻለ ወይም ችሎታ የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

6) ተቀጣሪው ሲሞት፣ ወይም

7) አሰሪው መስሪያ ቤት ባስቀመጠው የዲሲፕሊን ሥርዓት መሰረት ከስራ የሚያስወጣ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ሲወሰድ፡፡

## 13. ጥቅማ ጥቅም

1) በዚህ መመሪያ ከተገለጸው የደመወዝ ክፍያ ውጭ እንዲሁም በዚህ መመሪያ በግልጽ ከተቀመጠው ውጭ ለፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት የጊዜያዊ ሰራተኞች የጥቅማጥቅም ክፍያ ማድረግ አይቻልም፡፡

2) የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የጊዜያዊ ሰራተኞች ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የሚታይ ሆኖ ቀጣሪው መስሪያ ቤት ለስራው በተሳለጠ ሁኔታ መከናወን አስፈላጊ የሆኑ የስራ መሳሪያዎች እንዲያቀርብ ለቀጣሪ መስሪያ ቤቶች ግዴታ በጣለው መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፕሮጀክት ፕሮጀክት እንደሚለያይ ታሳቢ ተደርጎ ለፕሮጀክት ስራና አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ቁሳቁሶች፣ መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ መገልገያዎች እና ግብዓቶች ከፕሮጀክቱ ሰራተኞች የስራ ባህሪ እና የስራ ቦታ አንፃር አስፈላጊ እና አሳማኝ ሆኖ ሲገኝ እንደማንኛውም የፕሮጀክቱ ስራዎች በዕቅድ በፕሮጀክቱ በመያዝ በመስሪያ ቤቱ ከፕሮጀክቱ ወጪ በማድረግ ሊሟላ ይችላል፡፡

# ክፍል አራት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 14. የመመሪያው አፈጻጸም ክትትል ሥርዓት

1) ይህ የጊዜያዊ ሰራተኞች የደመወዝ ክፍያ አተገባበር መመሪያ በገንዘብ ሚኒስቴር እና በመስሪያ ቤቶች የውስጥ ኦዲት፣ በፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንዲሁም



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

በተመሳሳይ በክልል ደረጃ ኃላፊነት በተሰጣቸው ቢሮዎች እና ተቋማት አማካኝነት በአግባቡ ስለመተግበሩ ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡

2) የውጭ ኦዲተሮች የፌዴራል እና የክልል መስሪያቤቶችን ኦዲት ሲያደርጉ የመመሪያውን አተገባበር አስመልክቶ ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡

3) የፌዴራል እና የክልል መስሪያ ቤቶች የሰው ሀብት አስተዳደር ከሚመለከታቸው ሌሎች ክፍሎች ጋር በመቀናጀት መመሪያው በአግባቡ ስለመተግበሩ የማረጋገጥ እና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 15. <u>የተሻሩ መመሪያዎች</u>

በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መስሪያቤቶች በሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ለሚቀጠሩ ጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የደመወዝ ክፍያ አተገባበር መመሪያ ቁጥር 1046/2017 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 16. <u>መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ይፋዊ ድህረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ መጋቢት 2018 ዓ.ም
አህመዴ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

# ሰንጠረዥ 1

## የጊዜያዊ/ኮንትራት ሰራተኞች የደመወዝ ስኬል

| ደረጃ | የደመወዝ ዕርከን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| I | 6,125 | 7,166 | 8,208 | 9,249 | 10,290 | 11,331 | 12,373 | 13,414 |
| II | 6,598 | 7,720 | 8,842 | 9,964 | 11,085 | 12,207 | 13,329 | 14,450 |
| III | 10,719 | 12,541 | 14,363 | 16,185 | 18,008 | 19,830 | 21,652 | 23,474 |
| IV | 11,025 | 12,899 | 14,774 | 16,648 | 18,522 | 20,396 | 22,271 | 24,145 |
| V | 12,250 | 14,333 | 16,415 | 18,498 | 20,580 | 22,663 | 24,745 | 26,828 |
| VI | 14,700 | 17,199 | 19,698 | 22,197 | 24,696 | 27,195 | 29,694 | 32,193 |
| VII | 15,347 | 17,086 | 18,826 | 20,565 | 22,304 | 24,044 | 25,783 | 27,522 |
| VIII | 18,055 | 20,102 | 22,148 | 24,194 | 26,240 | 28,287 | 30,333 | 32,379 |
| IX | 21,242 | 23,649 | 26,056 | 28,464 | 30,871 | 33,278 | 35,686 | 38,093 |
| X | 24,990 | 27,822 | 30,654 | 33,487 | 36,319 | 39,151 | 41,983 | 44,815 |
| XI | 25,650 | 28,557 | 31,464 | 34,371 | 37,278 | 40,185 | 43,092 | 45,998 |
| XII | 26,640 | 29,660 | 32,679 | 35,698 | 38,717 | 41,737 | 44,756 | 47,775 |
| XIII | 27,701 | 30,392 | 33,083 | 35,774 | 38,465 | 41,156 | 43,847 | 46,538 |
| XIV | 29,400 | 32,256 | 35,112 | 37,968 | 40,824 | 43,680 | 46,536 | 49,392 |
| XV | 29,400 | 32,732 | 36,064 | 39,396 | 42,728 | 46,060 | 49,392 | 52,724 |
| XVI | 30,176 | 33,596 | 37,016 | 40,436 | 43,856 | 47,276 | 50,696 | 54,116 |
| XVII | 31,342 | 34,894 | 38,446 | 41,998 | 45,550 | 49,102 | 52,654 | 56,206 |
| XVIII | 34,627 | 37,990 | 41,354 | 44,718 | 48,082 | 51,445 | 54,809 | 58,173 |
| XIX | 43,283 | 47,488 | 51,693 | 55,897 | 60,102 | 64,307 | 68,511 | 72,716 |



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| XX | 54,104 | 59,360 | 64,616 | 69,872 | 75,128 | 80,383 | 85,639 | 90,895 |
| XXI | 84,197 | 92,377 | 100,556 | 108,735 | 116,914 | 125,093 | 133,272 | 141,452 |
| XXII | 105,247 | 115,471 | 125,695 | 135,919 | 146,143 | 156,367 | 166,591 | 176,815 |



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

# ሰንጠረዥ 2

## የጊዜያዊ/ኮንትራት ሰራተኞች የደመወዝ ስኬል

| ደረጃ | የደመወዝ ዕርከን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| I | 6,125 | 7,166 | 8,208 | 9,249 | 10,290 | 11,331 | 12,373 | 13,414 |
| II | 6,598 | 7,720 | 8,842 | 9,964 | 11,085 | 12,207 | 13,329 | 14,450 |
| III | 9,350 | 10,940 | 12,530 | 14,119 | 15,709 | 17,298 | 18,888 | 20,477 |
| IV | 9,800 | 11,466 | 13,132 | 14,798 | 16,464 | 18,130 | 19,796 | 21,462 |
| V | 11,025 | 12,899 | 14,774 | 16,648 | 18,522 | 20,396 | 22,271 | 24,145 |
| VI | 12,250 | 14,333 | 16,415 | 18,498 | 20,580 | 22,663 | 24,745 | 26,828 |
| VII | 14,068 | 15,662 | 17,257 | 18,851 | 20,446 | 22,040 | 23,634 | 25,229 |
| VIII | 16,551 | 18,426 | 20,302 | 22,178 | 24,054 | 25,929 | 27,805 | 29,681 |
| IX | 19,471 | 21,678 | 23,885 | 26,092 | 28,298 | 30,505 | 32,712 | 34,919 |
| X | 21,581 | 24,027 | 26,473 | 28,919 | 31,365 | 33,811 | 36,257 | 38,702 |
| XI | 22,161 | 24,314 | 26,467 | 28,619 | 30,772 | 32,925 | 35,078 | 37,231 |
| XII | 22,502 | 25,052 | 27,603 | 30,153 | 32,703 | 35,253 | 37,804 | 40,354 |
| XIII | 22,908 | 25,504 | 28,100 | 30,696 | 33,292 | 35,888 | 38,485 | 41,081 |
| XIV | 25,390 | 28,267 | 31,145 | 34,022 | 36,900 | 39,777 | 42,655 | 45,532 |
| XV | 26,473 | 29,474 | 32,474 | 35,474 | 38,474 | 41,475 | 44,475 | 47,475 |



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| XVI | 26,950 | 29,568 | 32,186 | 34,804 | 37,422 | 40,040 | 42,658 | 45,276 |
| XVII | 26,950 | 30,004 | 33,059 | 36,113 | 39,167 | 42,222 | 45,276 | 48,330 |
| XVIII | 27,701 | 30,392 | 33,083 | 35,774 | 38,465 | 41,156 | 43,847 | 46,538 |
| XIX | 34,627 | 37,990 | 41,354 | 44,718 | 48,082 | 51,445 | 54,809 | 58,173 |
| XX | 43,283 | 47,488 | 51,693 | 55,897 | 60,102 | 64,307 | 68,511 | 72,716 |
| XXI | 47,361 | 51,962 | 56,563 | 61,163 | 65,764 | 70,365 | 74,966 | 79,567 |
| XXII | 63,148 | 69,282 | 75,417 | 81,551 | 87,686 | 93,820 | 99,954 | 106,089 |



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

# ሰንጠረዥ 3

## የጊዜያዊ/ኮንትራት ሰራተኞች የደመወዝ ስኬል

| ደረጃ | የደመወዝ ዕርከን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| I | 6,125 | 7,166 | 8,208 | 9,249 | 10,290 | 11,331 | 12,373 | 13,414 |
| II | 8,575 | 10,033 | 11,491 | 12,948 | 14,406 | 15,864 | 17,322 | 18,779 |
| III | 9,800 | 11,466 | 13,132 | 14,798 | 16,464 | 18,130 | 19,796 | 21,462 |
| IV | 11,025 | 12,899 | 14,774 | 16,648 | 18,522 | 20,396 | 22,271 | 24,145 |
| V | 12,150 | 13,527 | 14,904 | 16,281 | 17,658 | 19,035 | 20,411 | 21,788 |
| VI | 14,294 | 15,914 | 17,534 | 19,154 | 20,774 | 22,394 | 24,014 | 25,633 |
| VII | 16,011 | 17,826 | 19,641 | 21,455 | 23,270 | 25,084 | 26,899 | 28,714 |
| VIII | 16,816 | 18,722 | 20,628 | 22,534 | 24,440 | 26,345 | 28,251 | 30,157 |
| IX | 16,972 | 18,896 | 20,819 | 22,743 | 24,667 | 26,590 | 28,514 | 30,437 |
| X | 17,701 | 19,707 | 21,714 | 23,720 | 25,726 | 27,732 | 29,738 | 31,744 |
| XI | 18,837 | 20,972 | 23,107 | 25,241 | 27,376 | 29,511 | 31,646 | 33,781 |
| XII | 19,784 | 21,706 | 23,627 | 25,549 | 27,471 | 29,393 | 31,315 | 33,237 |
| XIII | 19,968 | 22,230 | 24,493 | 26,756 | 29,019 | 31,282 | 33,545 | 35,808 |
| XIV | 20,825 | 23,185 | 25,545 | 27,906 | 30,266 | 32,626 | 34,986 | 37,346 |
| XV | 23,275 | 25,536 | 27,797 | 30,058 | 32,319 | 34,580 | 36,841 | 39,102 |



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.

# ሰንጠረዥ 4

## የጊዜያዊ/ኮንትራት ሰራተኞች የደመወዝ ስኬል

| ደረጃ | የደመወዝ ዕርከን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| I | 6,125 | 7,166 | 8,208 | 9,249 | 10,290 | 11,331 | 12,373 | 13,414 |
| II | 7,963 | 9,316 | 10,670 | 12,023 | 13,377 | 14,731 | 16,084 | 17,438 |
| III | 8,881 | 10,391 | 11,901 | 13,411 | 14,921 | 16,430 | 17,940 | 19,450 |
| IV | 9,800 | 11,466 | 13,132 | 14,798 | 16,464 | 18,130 | 19,796 | 21,462 |
| V | 12,683 | 14,121 | 15,558 | 16,996 | 18,433 | 19,871 | 21,308 | 22,746 |
| VI | 14,093 | 15,690 | 17,287 | 18,884 | 20,481 | 22,079 | 23,676 | 25,273 |
| VII | 15,275 | 17,006 | 18,738 | 20,469 | 22,200 | 23,931 | 25,662 | 27,393 |
| VIII | 15,659 | 17,433 | 19,208 | 20,982 | 22,757 | 24,532 | 26,306 | 28,081 |
| IX | 15,986 | 17,798 | 19,610 | 21,422 | 23,233 | 25,045 | 26,857 | 28,669 |
| X | 16,972 | 18,896 | 20,819 | 22,743 | 24,667 | 26,590 | 28,514 | 30,437 |
| XI | 17,398 | 19,370 | 21,342 | 23,314 | 25,286 | 27,257 | 29,229 | 31,201 |
| XII | 17,763 | 19,776 | 21,789 | 23,802 | 25,815 | 27,828 | 29,841 | 31,854 |
| XIII | 19,332 | 21,209 | 23,087 | 24,965 | 26,843 | 28,721 | 30,599 | 32,477 |
| XIV | 22,743 | 24,952 | 27,162 | 29,371 | 31,580 | 33,790 | 35,999 | 38,208 |



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 17th of March 2026.